የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የሳምንታዊ መረጃ ማሰራጫ

# ሳምንታዊ የቢዝነስ መረጃዎች

## በኢንፎሜሽንና ኮ/ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት

ከሐምሌ 25- ነሐሴ 2/2017
AUGUST1- 8, 2025 G.C

**1. በሕገ-ወጥ የውጭ ምንዛሪ የወንጀል ተግባር ላይ የተሰማሩ ተጠርጣሪዎች የባንክ ሂሳብ ታገደ**

ኢዜአ፡ ነሐሴ 2/2017

በሕገ-ወጥ የውጭ ምንዛሪ የወንጀል ተግባር ላይ የተሰማሩ 138 ተጠርጣሪዎች የባንክ ሂሳብ መታገዱን የፋይናንስ ደኅንነት አገልግሎት ገለጸ።

ሕጋዊና መደበኛ የባንክ ስርዓትን ወደ ጎን በመተው በህገ-ወጥ እና ትይዩ ገበያ የውጭ ምንዛሪ ወንጀል ላይ የተሰማሩ 138 ዋነኛ ተጠርጣሪዎች የገንዘብ እንቅስቃሴ እንዲታገድ ተደርጓል ብሏል።

የውጭ ምንዛሪ አገልግሎት በሕጋዊና መደበኛ የባንክ ሥርዓት በኩል እንዲከናወን በግልጽ የተቀመጠ መሆኑን ያወሳው መግለጫው፤ በሕገ-ወጥ መንገድ የምንዛሪ አገልግሎት ላይ የተሰማሩት ላይ ጠንካራ የሕግ ተጠያቂነት የሚያስከትል መሆኑን አስገንዝቧል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ በወንጀል ድርጊቱ ላይ ተሰማርቶ መገኘት የንብረት መወረስን ጨምሮ በከፍተኛ ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ በመሆኑ የንግዱ ማህበረሰብ መደበኛ የባንክ ስርዓትን እንዲጠቀም በመንግስት በኩል ማሳሳቢያ ሲሰጥ ቆይቷል ብሏል።

ሆኖም ግን አንዳንድ የንግድ ድርጅቶችና ግለሰቦች ህገ-ወጥ የውጭ ምንዛሪ ወንጀልን እንደ መደበኛ የንግድ ስራ በመያዝ ሲንቀሳቀሱ የነበሩ በመሆናቸው ክትትል ሲደረግባቸው ቆይቷል ሲል ገልጿል።

በዚሁ መሠረት ክትትል ተደርጎ የተደረሰባቸው እና በህገ-ወጥ የውጭ ምንዛሪ ላይ የተሰማሩ 138 ዋነኛ ተጠርጣሪዎች የገንዘብ እንቅስቃሴ እንዲታገድ መደረጉን ነው አገልግሎቱ በመግለጫው ያስታወቀው።

https://www.ena.et/web/amh/w/amh_7098979

**2. ለቡና ምርት እና ጥራት የተሰጠው ትኩረት የዘርፉን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ እያሳደገው ነው**

ኢዜአ፡ ነሐሴ 2/2017

ለቡና ምርትና ጥራት ትኩረት መሰጠቱ ዘርፉ እንዲያንሰራራ እና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታው እያደገ እንዲመጣ ማድረጉን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡና ማህበር አስታወቀ።

የማህበሩ ፕሬዚዳንት ሁሴን አምቦ (ዶ/ር) እንደገለጹት ባለፉት ዓመታት መንግስት ለቡና ምርትና ጥራት የሰጠው ትኩረት ዘርፉ እንዲያንሰራራ አድርጓል።

ይህም ከዘርፉ የሚጠበቀው ገቢ እያደገ እንዲመጣና አምራቹና ነጋዴው ተጠቃሚ እንዲሆኑ እያደረገ መሆኑን ጠቅሰው፣ በተያዘው በጀትም ይህን አጠናክሮ ለማስቀጠል ይሰራል ብለዋል።

https://www.ena.et/web/amh/w/amh_7096806

**3. አህጉራዊ የቡና ንግድ ዓውደ ርዕይ በአዲስ አበባ ሊካሄድ ነው**

ኤፍ.ኤም.ሲ፡ ነሐሴ 2፣2017

የአፍሪካ ቡና ንግድ ዓውደ ርዕይ ከጥር 27 እስከ 29 ቀን 2018 ዓ.ም በአዲስ ኢንተርናሽናል ኮንቬንሽን ማዕከል ይካሄዳል።

ለ22ኛ ጊዜ የሚካሄደው ዐውደ ርዕዩ የአፍሪካ ቡና ኢንዱስትሪ እድገትን ለማጠናከር እና በዘርፉ ዓለም አቀፍ የንግድ ትስስርን መፍጠር እንደሚያስችል ተመላክቷል።

ኢትዮጵያ በ2024 መርሐ ግብሩን ያስተናገደች ሲሆን፥ መንግስት አሁን ላይ ለዘርፉ የሰጠው ከፍተኛ ትኩረት በድጋሚ ለማስተናገድ እንድትመረጥ ማስቻሉ ተጠቅሷል። መድረኩ በአፍሪካ ልዩ ጣዕም ያላቸው ቡናዎችን በማስተዋወቅ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነታቸውን ለማሳደግ እንደሚያግዝም ተጠቁሟል።

በመድረኩ ከተለያዩ አፍሪካ ሀገራት የተወጣጡ የቡና አምራቾችና ላኪዎችን ጨምሮ ከ2 ሺህ በላይ የዘርፉ ተዋንያን እንደሚሳተፉ ይጠበቃል።

https://www.fanamc.com/archives/298563

**4. አንድ ዕቃ ከውጭ ለማስመጣት የሚያስፈልገውን የውጭ ምንዛሪ ለማግኘት ረዥም ጊዜ ይወስዳል››አቶ** ማሞ ምሕረቱ የብሔራዊ ባንክ ገዢ

ሪፖርተር፡ ነሐሴ 27፣2017 ዓ.ም የውጭ ምንዛሪ ግብይት በደላሎች ተፅዕኖ ሥር በመውደቁ አስመጪዎች መቸገራቸውንና ለተጨማሪ ወጪ መዳረጋቸውን ገለጹ።

በአስመጪነት ሥራ ላይ ብቻ የተሰማሩ ነጋዴዎች የውጭ ምንዛሪ ለማግኘት በባንኮችና በአስመጪዎች መካከል የድለላ ሥራ የሚሠሩ አካላት የሚጠይቁት ገንዘብ ከፍተኛ መሆንና ይህን ችግር ለመፍታ በባንኮች በኩል የሚደረግ ጥረት አለመኖር ሥራቸውን እንዳይሠሩ እያደረጋቸው መሆኑን ገለጹ።

በባንኮች የውጭ ምንዛሪ ለማግኘት በአንድ ዶላር ከሰባት ብር ጀምሮ ለደላሎች እንደሚከፍሉ በመኪና አስመጪነት ተሰማርተው የሚገኙት አቶ እዩኤል ፍስሃ ለሪፖርተር የገለጹ ሲሆን፣ ይህም ላኪዎች በባንኮች ያላቸውን የውጭ ምንዛሪ ለመጠቀም በባንኮችና የውጭ ምንዛሪውን በሚፈልገው አስመጪ መካከል በድለላነት ለሚሠሩ አካላት የሚከፈል መሆኑን ተጠቁመዋል።

https://ethiopianreporter.co

### 5. Ethiopian-Kenyan Investment Forum Unlocks New Business Opportunities

**ENA: August 6, 2025**

Ethiopia and Kenya are deepening their economic cooperation through the exploration of expanded business and trade opportunities.

The Ethiopian Embassy in Nairobi, in partnership with the Kenya National Chamber of Commerce and Industry (KNCCI), today hosted an investment and trade forum in Nairobi, to promote business opportunities in Ethiopia.

Over 150 representatives from various sectors attended the event, according to Ethiopia's Ministry of Foreign Affairs.

Deputy Head of Mission, Ambassador Demeke Atnafu, presented investment prospects in key sectors such as agriculture, manufacturing, mining, ICT, tourism, energy, and health care.

He also outlined the country's ongoing macroeconomic reforms, including the liberalization of telecom, banking, and foreign trade.

https://www.ena.et/web/eng/w/eng_7088404

### 6. Ethiopia Secures 120 Million USD from Meat, Offal Exports

**ENA: August 2, 2025**

The Ethiopian Livestock Development Institute (LDI) announced that the country earned 120 million USD from the export of meat and slaughter by-products during the past Ethiopian fiscal year.

Asrat Tera, Director General of the Institute, said the revenue growth was driven by sustained efforts to boost livestock production and improve earnings from the sector.

According to him, these efforts include enhancing animal breeds, training skilled professionals, and ensuring product quality.

Ethiopia currently exports 21 types of offal including liver, heart, kidney, and tongue in addition to meat, Asrat noted.

He also emphasized that over 22,620 tons of animal products were exported last fiscal year, marking a 53 percent increase compared to the previous year.

Saudi Arabia and the United Arab Emirates remain the primary markets for Ethiopian meat and by-products, he said, further elaborating that honey and beeswax were exported to countries such as Japan, Germany, and the United States.

https://www.ena.et/web/eng/w/eng_7069208

### 7. AfDB to Take Lead in USD 7.8bln Financing Mobilization Drive for Airport Megaproject

**The Reporter: August 9, 2025**

Ethiopian Airlines to finance 20 percent of costs out of pocket

The African Development Bank (AfDB) is set to lead efforts to raise USD 7.8 billion for the construction of a new international airport in Ethiopia, according to a formal announcement made this week.

A formal financing agreement between Prime Minister Abiy Ahmed (PhD) and AfDB outgoing President Akinwumi Adesina is scheduled to be signed on Monday, August 11, 2025. The deal will mark a major milestone in Ethiopia's longstanding efforts to build a new hub for its state-owned flag carrier, Ethiopian Airlines Group.

With the capacity to serve up to 100 million passengers annually, the Bishoftu International Airport slated for completion in three years is projected to become the largest on the continent.

The signing of the agreement would mark a major turning point in Ethiopia's most ambitious aviation infrastructure project to date and the announcement comes over a year after Ethiopian Airlines formally launched the project's design and financing process.

In August 2024, Ethiopian Airlines CEO Mesfin Tasew signed a design and consultancy contract with Dar Al-Handasah, a Beirut-based engineering firm.

The deal with the firm was finalized at the Ethiopian Skylight Hotel following a restricted international bid process involving 16 companies. The UAE based company, which previously worked on the Skylight Hotel and Bole terminals, was hired to design the 35 square-kilometer 'Airport City' near Obosirraa, in the Bishoftu area of Oromia Regional State.

https://www.thereporterethiopia.com/46386/

### 8. Minimum tax alternative sparks controversy among businesses

**Capital: August 3/2025**

The business community, particularly large taxpayers, has expressed concerns regarding the implementation of the newly enacted income tax proclamation.

The Ministry of Finance recently announced that the amended income tax law took effect at the beginning of the current budget year on July 8. However, taxpayers who spoke to Capital reported that tax authorities are insisting they file their profit tax declarations under the new proclamation, which aims to increase government revenue. Level A taxpayers—those in the highest tax bracket—reported that when they approached the tax authority to declare their profit tax for the previous budget year (which ended on July 7), their filings were rejected.

https://capitalethiopia.com/2025/08/03